**<u>“የኢትዮጵያ ህዝብ ብቸኛ ወዳጅ ኢሳያስ ኣፈወርቂ ብቻ ነዉ”</u>**

**ኤርትራና.ኮም**
**11 የካቲት 2002**

ተምረናል፡ ኣንብበናል የሚሉ ሰዎች፡ የኣእምሮ መዛባት በሽተኞች እስካልሆኑ ድረስ የሰብኣዊ ፍጡር የሞራል ደረጃ መለኪያዉ፡ ይናስም ይብዛ ለሰብኣዊ መብትና፡ ለፍትህ መርሆዎች የሚኖራቸዉ ግንዛቤ እንደሆነ የስነልቡና ጠበብት ይናገራሉ።

ዲሞክራሲ እግሩን ባልተከለበትና የፍትህ ጥያቄ እንደመብት ሳይሆን እንደነዉርና ወንጀል ወደተቆጠረበት የኤርትራ እዉነታ ተመልሰን በስልጣን ላይ ያለዉ፡ የፋሽሽት ኢሳያስ ኣገዛዝን ስንገመግም፡ ኤርትራዉያን ተረገምን እንዴ? ፋሽሽት ኢሳያስ ለጥፋትና ለቅጣት የተላከብን ሰይጣናዊ ሃይል ይሆን? ኣሊያም በኛ በኤርትራዉያን ሞኝነትና የዋህነት የተፈጠረ የጥፋት ሃይል ነዉን? ለሚሉት ኣመለካከቶች ተገዝተን፡ ኣንዱን ለመምረጥ በዉይይት ላይ በነበርንበት ወቅት፡ ኣንድ መሪ ታጋይ እንዲህ ብሎ ተናገረ፡ ጓዶች ኢሳያስ ከመጣበት ይምጣ፡ የፈጠረ ይፍጠረዉ፡ የህዝብ ጠላት ነዉ። የኢሳያስ የፋሽሽትነት ባህሪ ሊቀየር ኣይችልም። ፋሽሽትንም ኣቅፎ መኖር ስለማይቻል፡ የሚያዋጣዉ በተፋፋመ ትግል ገርስሶ ማስወገድ ብሎም ከኢትዮጵያዉያን ወንድሞቻችንና፡ እህቶቻችን ጋር እዉነተኛና ሰላምንና መከባበርን የሚያረጋግጥ ቁርጥ የሆነ ፍትሃዊ ኣመለካከት ኣሳድገን፡ ወደፊት ባሉበት ይለይለት ብለን መመረሽ ኣለብን እንጂ ብሶት ማሰማት ዋጋ የለዉም ብሎ ያሰማዉን ዲስኩር ሁሉ ግዜ እናስታዉሰዋለን። በደሴ ከተማ ዳዉዶ በተባለዉ ሰፈር በሰባት ድምጽ ብሌላቸዉ ጥይቶች፡ በኢሳያስ ማፍያዎች የተገደለዉ እዉቁ የፖለቲካ መሪ ዘካርያስ ንጉሰ። ለመንደርደርያ ያቀረብነዉን ሓሳብ እዚሁላይ ቀጭተን በቀጥታ ወደዋናዉ ጉዳይ ወደ ኣርእስታችን እንመልሳችሁ።

ኣቶ ንኣምን ዘለቀ፡ ኣቶ ስለሺ ጥላሁን፡ ኣቶ ፍቃደ ሽዋቀናና፡ ኣቶ ኢልያስ ክፍሌ፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ብቸኛ ወዳጅ ክቡር ፕረዚዳንት ኢሳያስ ኣፈወርቂ ብቻ ነዉ ፡ በኣሁኑ ግዜ በወያነ ግፍ የሚሰቃዩ ኢትዮጵያዉያን መጠለያ የሚያገኙት በኤርትራ ዉስጥ ብቻ ነዉ (2)፡ የኤርትራ መንግስት ለብዙ ሺ ኢትዮጵያዉያን ጥላ ሁነዋል። የኤርትራ ሚሊታራይዘሽን ምክንያት ወያኔ ነዉ፡ ወያኔ ባይኖር ኖሮ ኤርትራ ኣሁን ያለችበት ሁኔታ ላይ ኣትወድቅም ነበር። ወያኔ፡ ኢትዮጵያን ያለ ባህር በር ስላስቀራት፡ በዓመት 700 ሚልዮን ዶላር ለጅቡቲ ሳይሆን ላረቦች ያስረክባል። ኣልሸባብን የፈጠረዉ ወያኔ ነዉ ኢሳያስ ኣይደለም የሚሉትን ኣስተያየቶች በፓልቶክና፡ ነጻነት ለኢትዮጵያ በመባል ከሚታወቀዉ ሬድዮ ጣብያ በመቅረብ በፕረዚዳንት ኢሳያስ ላይ የታወጀዉን ማእቀብ ኢ-ፍትሃዊ ስለሆነ በተለይም ይህ ማቀብ ኤርትራ ዉስጥ ላሉት የኢትዮጵያ የተቃዉሞ ሃይሎችን ለማዳከም ያነጣጠረ ስለሆነ ማእቀቡን ከኢሳያስ ደጋፊዎች ጋር ኣብረን በመሰለፍ ተቃዉሞኣችንን ማሰማት ኣለብን በማለት ጥሪያቸዉን ለኢትዮጵያዉያን በማቅረብ ላይ ይገኛሉ።

ኣቶ ንኣምን ዘለቀና፡ ኣቶ ኢልያስ ክፍሌ በነጻነት ለኢትዮጵያ ሬድዮ ባልደረቦች የቀረበላቸዉን ጥያቄ መመለስ ኣቅቶኣቸዉ ሲንተባተቡና፡ የድሮዉን መርሳት ኣለብን፡ ኢሳያስ ኣፈወርቂ ዛሬ ሌላ ሰዉ ነዉ፡ ወደንም ጠላንም ኢትዮጵያ ያላት ወዳጅ እሱ ብቻ ነዉ በማለት ነጭ ሃሰት ሲያራምዱ ሰምተናል። ይህ ሃሰት ግን በራእይ ላይ ያላተኮረ፡ በመትከል፡ በእሴትና ስራ ምግባር ያልተነጻ፡ በግብ ላይ ያላነጣጠረ፡ በርሰ በርስ ግንኙነትና በቅራኔ ኣያያዝ ጥበብ ያልበሰለ ከመሆኑም ኣንጻር የነኣምንና የነ ኤልያስ ክፍሌን የፖለቲካ ድህነትና ኣለመብሰልን ያጋለጠ ኣጋጣሚ መሆኑን ነዉ የሚያሳየን እንጂ ኢትዮጵያዉያን በነዚህ የፖለቲካ ሀሁ በደንብ ባልቆጠሩ ግለሰቦች ተታለዉ፡ የተባበሩት መንግስታት በፋሽሽት ኢሳያስ ላይ የሰነዘሩትን ማዕቀብ ለመቃወም፡ ከኢሳያስ ደጋፊዎች ጋር ኣብረዉ ይሰለፋሉ ብለን በፍጹም ኣናምንም። እነ ንኣምንና ኤልያስ የፋሽሽት ኢሳያስ የግል ኣፍቃሪዎች ናቸዉ እንጂ፡ የኤርትራ ህዝብ ወዳጆች ኣይደሉም፡ እንዳሉት ማዕቀቡ በኤርትራ ህዝብ ላይ የታወጀ ኣይደለም፡ ማዕቀብ ብህዝብ ላይ ኣይታወጅም፡ የለም ኢሳያስ ማለት የኤርትራ ህዝብ ማለት ነዉ የሚሉን ከሆነ ደግሞ በኤርትራ ህዝብ ላይ መቀለዳቸዉን እንዲያቆሙ ነዉ የምናሳስባቸዉ።

ትንሽ ቁምነገር የሰራ የፖለቲካ ሰዉ፡ ብዙ ክብር ኣያገኝም። ትልቅ ጥፋት ቀርቶ፡ ትንሽ የፖለቲካ ጥፋት መስራት ግን ብዙ ዋጋ እንደሚከፈልበት በዓይናችን ኣይተናል። እና እነ ስለሺ ጥላሁን፡ ፍቃደ ሽዋቀና፡ ንኣምን ዘለቀና፡ ኤልያስ ክፍሌ የፋሽሽት ኢሳያስ ባንዳ መሆን የሚያኮራቸዉ ከሆነ ደስ ይበላቸዉ፡ የግል ትርፍና ዝናን ለማግኘት ፡ ኢሳያስ ኣፈወርቂ ኢትዮጵያዉያንን በማዳንና በመርዳት ላይ ያለ ነብይ ነዉ ብሎ ለማሳመን መሞከር ግን ቅዠት ነዉ። በተቃራኒ ኢትዮጵያዉያንን በጣም የሚያስቆጣና የሚያስቀይም ነገር መሆኑን በደንብ እንረዳዋለን። ይህ ዘግናኝ የፖለቲካ ስራ የሚያራምዱ ግለሰቦች ይቅር የማይባልለት ወንጀል መፈጸማቸዉ በኣጭር ግዜ ግልጽ እንደሚሆንላቸዉ ኣንጠራጠርም። ኣሁንም ቢሆን ግን በድፍረት የምንለዉ ነገር፡ የኢትዮጵያን ባንዴራ እያዉለበለቡ ፋሽሽት ኢሳያስን ለማዳን ከኢሳያስ ሚሊሻዎች ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘዉ የሚሰልፉ ኢትዮጵያዉያን ከጠቀስናቸዉ ግለሰቦች በስተቀር ሌሎች ይኖራሉ ብለን በተኣምር ኣናምንም።

እነ ነኣምን ዘለቀ፡ ኤልያስ ክፍሌ፡ ስለሺ ጥላሁንና፡ ፈቃደ ሽዋቀና፡ ከኢሳያስ ጋር እንዴትና ማን ኣገናኛቸዉ የሚለዉን ጥያቄ መመለስ በጣም ተገቢ ነዉ ብለን እናምናለን። እነዚህን ሰዎች የመለመሉትና ኣስመራ ድረስ ዘልቀዉ ከኢሳያስ ጋር ለተደጋጋሚ ግዜ እንዲገናኙ በር ከፋቾች ሁለቱ ሻለቃዎች ናቸዉ። ሻለቃ በርሄ ሃብተገርጊስና፡ ሻለቃ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ ተብለዉም የሚታወቁ ሲሆን የፋሽሽት ኢሳያስ ኣድናቂዎች፡ ወዳጆች፡ ኣማካሪዎችም ናቸዉ።

በዛሬዉ መጣጥፋችን ስለ ሻለቃ በርሄ ለመተቸት መርጠናል፡ በሌላ ግዜ ደግሞ ስለ ሻለቃ ዳዊት ወልደግዮርጊስ የምናዉቀዉን እንደምንጽፍ ቃል እንገባለን።

ሻለቃ በርሄ፡ በኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ጦርነት ግጭት ምክንያት፡ የኢሳያስን ወረራ በመደገፍ ብግሉ ብዙ ሺ ዶላር ከማበርከቱ በላይ፡ ወደ ባድመ ጦር ግንባር ጎራ ብሎ፡ ፋሽሽት ኢሳያስ ያስቆፈራቸዉን ምሽጎች ከጎበኘና ከፈተሸ ቦኃላ፡ በተለያዩ የህዝብ ስብሰባዎች እየተገኘ የባድሜን ምሽግ፡ የወያኔ ሰራዊት ቀርቶ ሌሎችም ሊሰብሩት ኣይችሉም፡ ኢሳያስ ጸሃይ ብርሃኔን ኣቋርጣለሁ ብትልምን'ኳ፡ ከባድመ ፈጽመን ኣንወጣም ማለቱ ትክክል ነዉ እያለ መሰበኩን ሰምተናል። የጦር ሜዳ ኤክስፐርት ነኝ ባዩ ሻለቃ በርሄ ስለ ባድመ ምሽጎች ያቀረበዉ ጥናት የተሳሳተ ስለ መኖሩን መግለጫ ኣቅርቦ ኣያዉቅም። ሓቁን ሳይወድ ዉጦ ዝምነዉ ያለዉ፡ ወዲያዉኑ ግን ከፋሽሽት ኢሳያስ ኣዲስ ኣሳይመንት ለመቀበልና፡ በኤርትራዉያን ወጣቶች ላብና ድካም፡ እንዲሁም በነጻ ጉልበት የተሰራዉን ቪላዉን ለመጎብኘት ወደ ኣስመራ መመላለስ ጀመረ። የተሰጠዉ ስራ ደግሞ በዉጭ ኣገር ያሉትን በሃይለስላሴም ይሁን በደርግ ግዜ መለዮ ለባሾች የነበሩትናን እንዲሁም ከወያኔ ጋር የከረረ ቂም ያላቸዉን ግለሰቦች ለማሰባሰብና ትጥቃዊ ትግል ለማካሄድ በፋሺሽት ኢሳያስ የረቀቀዉን ፕላን እያሳየ ኢሳያስ ለማስታጠቅም ይሁን ሁሉም እገዛ ለማድረግ ዝግጁ ነዉ፡ ለማረጋገጥ የሚፈልግ ካለም፡ በኢሳያስ ወጪ ኣስመራ መግባትና መዉጣት ይችላል፡ ከፕረዚደንት ኢሳያስ ጋርም መነጋገር፡ መመካከር ይቻላል እያለ ነገሮችን ግልጽ በማድረግ በየተራ እነ ነኣምን ዘለቀን፡ እነ ስለሺ ጥላሁንን፡ እነ ኤልያስ ክፍሌን ወደ ኣስመራ እየላከ፡ ኢሳያስ የኢትዮጵያ ወዳጅ ነዉ፡ በጋራ ለጋራ ጥቅም ዋናዉን ጠላት ወያኔን እናስወግድ እያለ ኢትዮጵያዉያንን ሲሰብክ፡ ኤርትራዉያንን ደግሞ፡ ኦሮሞ ተነስተዋል፡ ኣማራም ኣሁን እየተነሳ ነዉ፡ ወያኔ በጠላት ተከበዋል፡ በሱማሌ፡ በኦሮሚያ፡ ብኡጋዴን በቃ ወያኔ በጠላት ተከበዋል። የትግራይ ልጆች ሳይቀሩ ወያኔን ለማፍረስ ቆርጠዉ ተነስተዋል እያለ ላለፉት ስምንት ዓመታት የዉሸት ጥሩንባዉን የነፋና እስካሁንም ድረስ በመንፋት የሚገኝ ስነስርዓት የሌለዉ እዉቅ የኣለማችንና ብርቅ የኣፍሪቃ ተወላጅ የሆኑትን የቀድሞዉን የተባበሩት መንግስታት መሪ ኮፊ ኣናንን በህዝብ ስብሰባ ላይ ሞኝ ብሎ የተሳደበና ያዋረደ፡ ስድና በርጅና እድሜዉ ከመከበር ይልቅ ዉርደትን የሚሻ ባለጌ ሰዉ ነዉ። ኮፊ ኣናንን የሰደበበት ምክንያት፡ ኮፊ ኣናን ፋሽሽት ኢሳያስን ስላስጠነቀቁ ብቻ ነዉ እንጂ ሌላ ምንም ምክንያት የለዉም።

ይህ ሞኝ የሆነ ሻለቃ ትናንት ከፋሽሽት ኢሳያስ ጋር ኣብሮ ኢትዮጵያን መዉጋቱን ረስቶ፡ ኣሁን ለጋራ ጥቅም ወያኔን እናስወግድ፡ ፕረዚዳንት ኢሳያስ የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስከበር ዝግጁ ነዉ፡ ኢሳያስ ለኢትዮጵያ ኣንድነት ተቆርቋሪ ነዉ እና በጋራ ሰልፍ ወጥተን ማፅቀቡን እንቃወመዉ እያለ የፋሽሽት ኢሳያስን የስልጣን ዕድሜ ለማራዘም ሽርጉድ ማለት ከጀመረ ሰንብተዋል። የፋሺሽት ኢሳያስ ደጋፊዎች ብቻቸዉን ወደ ሰልፍ መዉጣት ስላስፈራቸዉ

የኢትዮጵያና የሶማሊ ባንዴራ የሚያዉለበልቡ ግለሰቦችን በብርም ቢሆን ገዝተዉ ለማሳለፍ ኣሊያም ራሳቸዉ የኢትዮጵያና የሱማሌ ባንዴራ በማዉለብለብ የሰልፍ ድራማ ለመስራት ዝግጁ መሆናቸዉን ደርሰንበታል።

ሻለቃ በርሄ፡ ኤልያስ ክፍሌ ባዘጋጀለት ፓልቶክ ቀርቦ፡ ትርጉምና ዉጤት የሌለዉ ስራ ነዉ የሰራዉ። በክፍሉ ዉስጥ የነበሩት ሰዎች ቁጥር 200 ብቻ ነበር። ከነዚሁም 80% የኢሳያስ ደጋፊዎች የሆኑ ኤርትራዉያን መሆናቸዉን ኣረጋግጠናል 15% ደግሞ የኤርትራ ተቃዋሚዎች እንደነበሩ ለኛ ግልጽ ሆነዋል። የቀሩት 5%፡ ኢትዮጵያዉያን ነበሩ ብለን ጥናታችንን ኣጠናቀናል። ሞኙ ሻለቃ ግን ከማን ጋ እንዳመሸ ኣልገባዉም፡ ኢትዮጵያዉያንን ያገኘ መስሎት ኣሁን እንተጋገዝ ኣብረን ሰልፍ ላይ እንገኝ፡ ልዩነቶቻችንን ቀርፈን በሰላምና በመከባበር የምንኖርበት ግዜ ሩቅ ኣይደለም እያለ ለቅሶዉን ይልቀቀዉ እንጂ፡ ፉሽሽት ኢሳያስን ለማዳን ፍቃደኛ የሚሆኑ ኢትዮጵያዉያን ማግኘት ማሰብ የቀን ህልም መሆኑን ማወቅ ኣለበት። የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ ንኣምን እንዳሉት፡ ከኢሳያስ በስተቀር ወዳጅ የሌለዉ ህዝብ ኣይደለም፡ የኢትዮጵያ ህዝብ በዓለም ዉስጥ ብዙ ኣድናቂና ወዳጅ ያለዉ ጨዋ ህዝብ ነዉ።

በኢትዮጵያዉያን መካከል የፖለቲካ ልዩነቶች መኖራቸዉን በደንብ እናዉቃለን፡ ሆኖም ግን ኣገራቸዉን ኣሳልፈዉ እስከመስጠት ድረስ የሚያደርስ ልዩነቶች ኣሉዋቸዉ ብለን ኣናምንም። ኢሳያስ ኣፈወርቂ የኢትዮጵያ ብቸኛ ወዳጅ ነዉ ብሎ ማመንም ይሁን ሌሎችን ለማሳመን መሞከር ኢትዮጵያን መካድ፡ ኢትዮጵያን ማድማት ካልሆነ በስተቀር ሌላ የፖለቲካ ትርጉም ሊሰጠዉ ኣይችልም።

በመጨረሻም፡ ማዕቅቡ ብምንም ተኣምር በሰልፍ ሊቀየር ኣይችልም። በሰልፍ የተቀየረ ማዕቀብ ኣይተን ኣናቅም፡ ማዕቅቡ ሊቀየር የሚችለዉ ፉሽሽት ኢሳያስ ኣልሸባብን ማስታጠቁ ሲያቆምና፡ እንዲሁም ወሮ ከያዘዉ የጅቡቲ መሬት ጭራዉን ይዞ ሲወጣ ብቻ ነዉ እንጂ በባራክ ኦባማ መኖርያ ፊት ለፊት ባለዉ ቦታ ከበሮና እስክስታ በመምታት ኣይደለም።

ኤርትራና ኢትዮጵያ ለዘላለም ይኑሩ

ኤርትራና.ኮም
11 የካቲት 2002